EthioLion



# ሰሞኑን በፓልቶክ

## ቁጥር ፲፩

ከበልጅግ አሊ

ሰሞኑን በፓልቶክ የሚለውን ተከታታይ ርዕሴን ለአንባቢያን ማቅረብ ከተውኩ ሰነበትኩ ።መቼም ከፓልቶክ የሚገርም ነገር ጠፍቶ አያውቅምና እንደገና ላነሳው ቻልኩ ። ጉዳዩም ሰሞኑን በፓልቶክ የሰማሁት ቃለ መጠይቅ ነው።። ከኢሕአፓ የወጡት አንጃ መሪዎች በፓልቶክ ቀርበው የተናገሩት (እንደ ስድብ አይቆጠርብኝ እንጂ ) ውሸት እንዲሁ ላልፈው አልፈለግሁም ። በተለይ አንደኛውን በሁለት ምላስነት በተለያየ ወቅት ሰላገኘኋቸው ገርሞኛል ።የዛሬ አስራ ሦስት ዓመት ግድም ኢአግ የሚሉት ድርጅት በተቋቋመ ጊዜ የድርጅቱ ሊቀመንበር ሆነው ወያኔን ለማውረድ ሰላማዊ ትግል ማለት ከወያኔ ጋር መሞዳሞድ ነው ብለውን ነበር ።አሁን ደግሞ የሰላሙ ትግል ርግብ ያዥ ነኝ ብለው ሰማኋቸው ። ይህንን ሳስበው አንድ ወዳጄ ያጫወተኝ ጉዳይ ትዝ አለኝ ።

ሰውየው ውሸታም ነው ።ሃገሩ ሻሸመኔ ነው። ምስክርነት ተጠርቶ ፍርድ ቤት ይቀርባል ። የተከሳሽ ጠበቃ የምስክሩን ውሸታምነት ያውቃል ። ይህንን ለዳኛው ለማስረዳት “ውሸታም ነህ “ ከማለት ይልቅ ዘዴ መጠቀም ፈለገ ፤

“ስምህ ማነው“ ? ብሎ ጠበቃውን ምስክሩን ጠየቀው ፣
“አበበ“ ብሎ መለሰ ።
“ሃገርህ የት ነው?“
“ደብረዘይት“ ብሎ መለሰ።

ጠበቃው ሌላ ብዙ ጥያቄዎች ሲጠይቅ ቆይቶ እንደገና መለስ አደረገና ውሸታሙን ምስክር “ሀገርህ የት ነው ?“ ብሎ ጠየቀው ።
ምስክሩም ያለ ምንም አለማመንታት ፤

“ናዝሬት አለ “ ። መቼም ውሸት ይረሳልና ሳተ።

ይህንን ውሸት የሰሙት ዳኛ “ምነው ቅድም ደብረዘይት ብለኸን ?“ ብለው በመገረም ሲጠይቁት ፤

ጠበቃው “ምነው ጌታዬ ባይቸኩሉብኝ ሃገሩ ሻሸመኔ ሳላገባው አልቀርም ነበር እኮ ! “ አለና ፍርዱን ለመስማት የተሰበሰበውን ሕዝብ አሳቀ ይባላል።

ከዚህ የበለጠ ሰለ ቃለ መጠይቁ የምለው አይኖረኝም ። እነዚህን ግለሰቦች ወደፊት ቃለ መጠይቅ የምትጠይቁ ሁሉ ኢአግ ( የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር ) ይባል ሰለነበረው ድርጅት መነሻና ፣ መጨረሻ ሳትጠይቁ እንዳታልፉብኝ አደራዬ የጠበቀ ነው። በጋዜጠኛ ሞያ በሰል ያላችሁ ደግሞ ሱዳን ያሉትን የኢአግ አባላት እንድታነጋግሯቸው አሳስባለሁ ። ምንም እንኳ ለዘመኑ የፓልቶክ ፖለቲካ የሚጥም ወሬ ባይኖራቸውም እውነት ተደብቃ ትገኝ ይሆናልና መበርታት ያሻል። ግን ድምፅ ለሌለው ማን ይናገርለታል?። እኔ የማስጠነቅቃችሁ ጉዳይ ቢኖር ይህ የእውነት ፈለጋ ጉዞ ስትጀምሩ “ የለውጥ አጋች “ የሚል ማዕረግ እንደሚሰጣችሁ ከወዲሁ ላሳስባችሁ እወዳለሁ ።

Ethiopia will prevail !

ሕሊናቸውን ባይሹት ፤ ኀዘን የሚሱት እነሱ
ለሰባት እምነት ሲምሉ ፣ በሰባት ምላስ ሲያወሱ
ባንደኛው ሲነካከሱ
በሦስተኛው ሲካሰሱ
ሌት ዓይኑን ላፈር ያሉትን ፣ሳይነጋ የሚያወድሱ
እነርሱን አድርጎብን ጨዋ፤ የሸንጎ የባሕል አዋይ
የሥነ- ሥርዓት ደላዳይ
መራጭ ቆራጭ ቀናን ከአባይ
ጨዋ መሳይ ፤ ንፁህ መሳይ
ከእኔ ላይሻሉ ፤ እኔን ምንትስ ባይ ።

**ማነው. . . . . ምንትስ?**
**ፀጋዬ ገብረመድህን ( ሎሪያት )**
**እሳት ወይ አበባ ከመለው መፀሐፍ የተወሰደ።**

ሌላው ደግሞ በጣም የገረመኝ በሬዲዮ የተሰጠ ምልልስ ነው ።ከኢሕአፓ የወጡ አንጃ መሪ የሆኑ ግለሰሰብ ሰለኢሕአፓ ተጠይቀው ነበር። መልሳቸው የአስተሳሰባቸውን አድማስ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ።

**“ኢሕአፓ ይላሉ ( የራሳቸውን ድርጅት እንደ ኢሕአፓ ወስደው ) በመከፋፈሉ ምክንያት ተጠናክሯል ። ዛሬ ከመቼውም በላይ ጠንካራ ነው።“**

ብለው እርፍ አሉ ። መከፋፈል መጠናከር ከሆነ ስለሕብረት ከሁሉም ጋር መተባበር ያስፈልጋል ብለው ያሉት የሚያስቅ ነው ማለት ነው። ይህ መልሳቸው ሌላ አንድ በእውነት የተፈፀመ ታሪክ አስታወሰኝ።

በአንድ ወቅት የምሰራበት መስሪያ ቤት ውስጥ አንድ ሠራተኛ ነበር ። ይህ ሰው ለመማር ብዙ ይሞክር ነበር ።ተመኝቶም አልቀረ መሠረተ ትምህርት እንደተጀመረ ተማረና ማንበብና መፃፍ አወቀ ። የመሥሪያ ቤቱ ሃላፊዎች እንደ ሽልማት አድርገው በቆሎ ከሌላ ቦታ በቅናሽ ዋጋ ገዝቶ አምጥቶ ለሠራተኛው እንዲያከፋፍል ተደረገ ። ታዲያ ከተማ መመላለስ ሲጀምር ሌሎች ነገሮች ለመደና ገንዘብ አጉድሎ ታሰረ ። ይህ ትኩስ ዜና በዛች ትንሽ መንደር እንደተሰማ ጠጅ ቤት ውስጥ እንዲህ ተብሎ ተዘፈነ ።

**መደመር ሳይማር መቀነስ ተምሮ**
**ያ ታደሰ ውቤ ሄደ ተጠፍሮ ።**

መደመርን የማያውቅ ሰው መቀነስ ከቻለ አደጋ ላይ ይወድቃል ። በአውሮፓ የነበረውን ኢሕአፓ በመቀነስ ጀምረው ፣ ቀጥለውም እራሳቸውን ከኢሕፓ ቀነሱ ።በእውነቱ ግን ያንን ሠራተኛ ያበላሹት ከዐቅሙ በላይ ሃላፊነት ያሸከሙት የመሥሪያ ቤቱ ሃላፊዎች ናቸው ። ከዚህ በላይ ገንዘብን ሰለማጉደል በተረኩት ታሪክ የኢሕአፓ አባላት የቀድሞዎቹም ይሁን የአሁኖቹ በአብዛኛው ድምፅ የሚደግፉኝ ይመስለኛል ።ሰለዚህ መከፋፈል ፣መለያየት፣መበታተን ጥንካሬ ለመሰላቸው አመለካከት ትንሽ ለሆኑ ግለሰቦች የምላቸው ነገር ቢኖር ምን አልባት ይህ የግለሰቦችን ጊዜያዊ የሥልጣን ጥማት ያረካ እንደሆን እንጂ ለሃገራችን ፋይዳ የለውም ።ችሎታ የሌላቸውን ግለሰቦች ከዐቅማቸው በላይ የሆነ ሥልጣን መስጠት ከወያኔ ጋር የሚደረገውን የትግል ጉዞ ፍታት ያደርገዋል እንጂ በቅርብ ጊዜ ዴሞክራሲያዊ የሆነች አገር አይመሰርትልንም ።

የገባችሁ ገባችሁ ፤ ያልገባችሁ በሌላ ርዕስ እስክንገኛ ሰለኛ የሚያስብ በሰላም ይክረም ብላችሁ ምን ይመስላችኋል ?

በልጅግ አሊ
ይህንን ፅሁፍ በሚመለከት ሀሳብ መስጠት ለምትፈልጉ በዚህ ኢሜል አድራሻ ተጠቀሙ።
beljig.ali@gmail.com